Global Amhara Coalition

United States of America

1103 Amherst Avenue, Suite 2

Silver Spring, MD 20902

መጋቢት 12 ቀን 2013 ዓ ም

ለኦሮሚያ ክልላዊ  መንግሥት ምክትል  ርእሰ መስተዳደር፣ አቶ ሺመልስ አብዲሳ

ከዓለም አቀፍ የአማራ ህብረትና  በውጭ ከሚኖሩ ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን

ጉዳዩ፤በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በማያባራ መልኩ አማራው በአማራነቱ  እየደረሰበት ያለውን
የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ (Genocide) ለማውገዝና በአስቸኳይ እንዲቆም መጠየቅን ይመለከታል::

እኛ በውጭ የምንኖር ትውልደ አማራ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም የሰው ልጅ በህይዎት የመኖር የማይገሰስ መብት መከበር የምናምን ኢትዮጵያውያን ሁሉ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ በኦሮሚያ ክልል “ኦነግ ሸኔ"በተባለ ቡድን ሽፋን የሚንቀሳቀሰው የታጠቀ የኦነግ ኃይልና በክልሉ መንግስት መዋቅር ድጋፍና ቀጥተኛ ተሳትፎ አማራው በአማራነቱእየተፈፀመበት ያለውን ዘግናኝና አሰቃቂ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ (Genocide) አጥብቀን እናወግዛለን::  በአስቸኳይ እንዲቆምም በአፅንዖት እንጠይቃለን:: ከዚህ ጋር በተያያዘ፣  እኛ ፈፅሞ ሊገባንና ልንረዳው ያልቻልነው ነገር አማራው በደሙና በአጥንቱ ከመሰረታት አገሩ፣ከኢትዮጵያ ወጥቶ የት እንዲሄድ ተፈልጎ ነው ይኸ ሁሉየማያባራ እልቂት እየተፈፀመበት ያለው?
ትህነግ ኦሮሚያ ብላ ካዋቀረችው የኢትዮጵያ ክፍለ ግዛትአማራውን ለማፅዳት በትህነግና  በኦነግ ዘመቻ ከተከፈተበት ሦስት አስርተ አመታት ቢያስቆጥርም ነገር ግን እንደ አለፉት ሦስት አመታት በተለይም  እርሰዎ የክልሉ ምክትል ርእሰ መስተዳደር ሆነው ከተሾሙ ጊዜ ወዲህ በአማራው ላይ እየተፈጸመ እንዳለው ዘግናኝና የተቀነባበረ የዘር ማጥፋት  ዘመቻ ተካሂዶበት አያውቅም:: እንደ ምሳሌለመጥቀስ ባለፈው አመት ጥቅምት ወር አቶ ጃዋር ሲራጅ መሀመድ በመንግሥት  የፀጥታ ኃይሎች ተከበብሁ ያለውን እወጃ ተከትሎ በአርሲ ፣ በባሌ፣ በሀረርጌና በወለጋ በአማራውና ኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ክርቲያን ኢትዮጵያውያን ላይ በተቀነባበረ መልኩ የተካሄደወን አረመኔአዊ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ በመሪር ሀዘንና ቁጭት የምናስታውሰው ነው::እንዲሁም ባለፈው አመት ሰኔ ወር ላይ የአርቲስት ኃጫሉ ሁንዴሳን  መገደል እንደ ሰበብበመጠቀም ከፍተኛ ዝግጅት የተደረገበትና መንግስታዊ የስራ ኃላፊወች የተሳተፉበት በአርሲ፣ ሻሸመኔ ፣ባሌ

ና ሀረርጌ እንዲሁም በወለጋ በአማራውናበኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች የተፈፀመው የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ መቼ ም የሚረሳ አይደለም:: የክልሉ የመንግሥትአካላት ለመሳተፋቸው ብዙ ማስረጃወችና መረጃዎች አሉ::
ለምሳሌ በባሌ የተወሰኑ የክልሉ የፓሊስ አባላትመሳሪያቸውን ለአራጆች በመስጠት በቀጥታ የተሳተፉ ሲሆን፤በአርሲና በሻሸመኔ ደግሞ በቂ ኃይል የለንም፤ ትእዛዝአልተሰጠንም በሚል ሺፋን አይናቸው እያየ አማራውና ኦርቶዶክሱ ሲታረድ ንብረቱ ሲዘረፍና ሲቃጠል ዝም ብለው በስላቅ የተመለከቱትና አንዳንዶችም የፀጥታ አካላት እልቂቱንና የንብረት ቃጠሎውን በስልካቸው እየቀረፁት እንደነበር በሚዲያ ተዘግቧል ::
ከፍተኛ የክልሉ አመራሮችም ትእዛዝ እንዲሰጡ በከተማ አስተዳደር አመራሮች ሲጠየቁ
አርፈህ ተቀመጥ የሚል መልስ እንደተሰጣቸው ለመረዳት ችለናል::
ከዚህ የሰኔው ጭፍጨፋ የተረፉትም ሰወች እንደገለፁት ጭፍጨፋው ከመደረጉ ከቀናት በፊት ቤት ለቤት ፍተሻ በማድረግ አማራዎችናኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችን ለይተው እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ለመጠበቅ የታጠቁትን መሳሪያ በመንጠቅ ለጨፍጫፊወች ምቹ ሁኔታ እንደፈጠሩላቸው ተረድተናል:: እንደዚሁም በዚህ ዓመት
ጥቅምት ወር በቄለም ወለጋ በአማራወች ላይ የደረሰው የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ሁሉንም ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ሰው የሆነ ፍጡርን ሁሉ እጅግ ያሳዘነና ከዚህ በሁዋላ የትም አይደገምም ተብሎ የታመነበት ነበር:: ይህ ጭፍጨፋ ከመፈፀሙ በፊት በአካባቢው ሰፍሮ የነበረው የመከላከያ ሰራዊት በስልት እንዲወጣ ተደርጎ ወዲያው ጨፍጫፊወች አካባቢውን በመቆጣጠር ህዝቡን ለስብሰባ ጠርተው ፈጅተውታል:: በዚህ አልበቃ ብሎ በወለጋ በሆሮ ጉድሩ ወረዳ በተለያዩ አካባቢወች ለቁጥር በሚያዳግት መልኩ በአማራወች ላይ እየደረሰ ያለው የዘርማጥፋት እልቂት የሁላችንንም ትዕግስት ያስጨረሰ ጉዳይ ሆኗል:: ይባስ ብሎ ከኦነግ ታጣቂ ቡድን ጭፍጨፋ ያመለጡትን አማራወች የኦሮሚያ ልዩ ኃይልእየገደላቸው እንደሆነ ከጭፍጨፋው ከተረፉ ዕማኞች ለማወቅ ችለናል:: አማራው ከማንኛውም ገዳይ ቡድን ራሱን ሊከላከልበትየገዛውን መሳሪያ የኦሮሚያ ልዩ ኃይል አስገድዶ በመግፈፍ በእቅድ መሰረት በተዘጋጁ ገዳይ ቡድኖች እያስጨረሰው ይገኛል:: ከጨፍጫፊው ቡድን የተረፈውን ደግሞ ራሱ ልዩ ኃይሉ ዕየጨረሰው ይገኛል:: የኦሮሚያ ልዩ ኃይል በክልሉ መገናኛ ብዙሀን እንደሚነገረው ኦነግ ሸኔን እየተዋጋ ሳይሆን አማራውን በመግደልና በማሳደድ ላይ ተጠምዶ እንደሚገኝ ብዙ ማስረጃወች አሉ::
በወለጋም እንደሚፈፀመው በመተከልም በአማራወችና አገወች ላይ ዕየተፈፀመ ባለውየዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ የኦሮሚያ ክልል መንግስታዊ መዋቅርበእጅ አዙር እየተሳተፈበት ለመሆኑ ብዙ አመላካች መረጃዎች እየወጡ መሆኑን እንረዳለን:: በአማራው ላይ እንደዚህአይነት የማያባራ ዘግናኝ ጭፍጨፋ እየተፈፀመ በርሰዎ የሚመራው የክልሉ መንግስት እንዲሁም በኦሮሚያብልፅግና የሚዘወረው የፌደራሉ መንግስት ይህንን ዘግናኝ የዘር ማጥፋት ዘመቻ
ከዛሬ ነገ ያስቆመዋል በሚል ተስፋ እስከ ዛሬ በትዕግስት ስንጠብቅ ነበር:: ነገር ግንአልሆነም:: ከዚህ በሁዋላ በአስቸኳይ የማያዳግም እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጉ ዘንድ አጥብቀን እንጠይቃለን::
አማራው ላይ እየተካሄደ ላለው መጠነ ሰፊ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ዋነኛ ተጠያቂው እርሰዎ የሚመሩት የክልሉ መንግስትና እንዲሁምበጠቅላይ ምኒስትሩ የሚመራው የፌደራሉ መንግሥት ናቸው::
ለመሆኑ አማራውን ከሌላውኢትዮጵያውያን ጋር በእኩልነት የማታይ ኢትዮጵያ መኖር ትችላለች የሚል ዕሳቤ ካለ ፍፁም ስህተትና የማይቻል መሆኑን ከወዲሁ ልናስገነዝብ እንወዳለን:: የሚሻለውና መሆንም ያለበት ትህነግ በተንኮል የዘራችውን አማራጠል የተሳሳተ ትርክት በመቅበር ሁሉም ኢትዮጵያዊ በዜግነቱ በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል በባለቤትነትና በእኩልነት የሚኖርባትን አገር ዳግምማረጋገጥ ነው:: ኢትዮጵያውያን ከጥንት ጀምሮ የሚያምርባቸው ህብረታቸውና አንድነታቸው ነው:: ኦሮሞው ከሌሎችወንድምና እህቶቹ ጋር ተባብሮ በርካታ ድሎችን ሲአስመዘግብ ኖሯል :: ለአብነት ከሚጠቀሱት ጎልቶ የሚታየው አንፀባራቂው የአድዋ ድል ነው::
በዘመናችን ደግሞ ሁለተኛ አድዋበመባል የሚታወቀውን የካራማራን ድል ተቀዳጅቷል፤በቅርቡ በጭካኔው በታሪክ አምሳያ የሌለውን ጸረ-ሕዝብ፤ ጸረ-ዲሞክራሲ፤ ጸረ
ፍትህ፤ ጸረ አብሮነት፤ የሃገር ከሃዲና ዘራፊ የሆነውን ትህነግንም በማንበርከክ ላይ
ይገኛል።ይህ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን የሚያኮራ የድል ታሪክ እንዳለ ሆኖ ግን፤በዐማራው ንጹህና ሰርቶ አደር ሕዝብ ላይ ግን በተከታታይ የሚካሄደው ብሄር ተኮር እና ማንነትን መሰረት ያደረገ ጥቃትና እልቂት ፣ መፈናቀል

ምንም አላቆመም። ከላይ እንደተጠቀሰው ይህ እልቂት በወለጋ ጎልቶ ይታያል። ለማነጻጸር ያህል ኦሮሞኢትዮጵያውያን በአማራው ክልል ማንነታቸው ተከብሮ የራሳቸው የዞን አስተዳደር መስርተው በቋንቋቸው እየተማሩና እየተዳኙ እንደ ልባቸው ተንቀሳቅሰው ሰርተውና ተከብረው ይኖራሉ:: ምነው አማራው ተመሳሳይ መብትና ክብር በኦሮሚያ ክልል እንዲያገኝ አይደረግም?

ትህነግን በአጭር ጊዜ ለመቆጣጠር የቻለው የኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት እንዴት በወለጋና በቤኒሻንጉል ጉምዝ በተከታታይ ለሚካሄዱት ብሄር ተኮር እልቂቶች ትኩረት ሰጥቶ ሊቆጣጠራቸውአልቻለም? የሚለው ጥያቄ መላው ዓለምን እያነጋገረ መሆኑን እንደሚረዱት እናምናለን።

ይህን አስመልክተን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግስትና ለፌደራል መንግስት እናቀርባለን::

1. የኦሚያ ፖሊስና ልዩ ኃይል በዐማራው ላይ የሚካሄደውን ተከታታይ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ለማስቆም ለምን አልቻለም?

2. የዐማራው ነዋሪ ሕዝብ የራሱንና የአካባቢውን ደህንነት ለመጠበቅና ለማስከበር በራሱ ወጭ የገዛውን መሳሪያ ለምን የክልሉና የፌደራሉ መንግሥት ገፈፉት ወይንም ነጠቁት?

ይህ ጥሮ ግሮ የሚኖር ሕዝብ መሳሪያውን በንጹህ ወገኖቹ ላይ ጉዳት ያደርሳል የሚል ስጋት ካለ ስህተት ነው:: አማራው የዚህ ዐይነት ታሪክና ስነልቦናም የለውም፤ ስነ ልቦናው፤ እምነቱናኢትዮጵያዊነቱ አይፈቅድም።

3. ትህነግ ከሞት አፋፍ ሆኖ ራሱን ለማዳን በተከዜ በርሃ እየባዘነ በሚግኝበት በአሁኑ ጊዜ በወለጋ በአማሮች ላይ የሚደርሰውን ጭፍጨፉ ትህነግ አደረገው ማለቱ ከማን ተቀባይነት ለማግኘት ነው?

መፍትሄስ ያመጣልን? ትህነግዐማራው እንዲጨፈጨፍ ማኒፈስቶ አውጥቶ ጭፍጨፋ አካሂዷል። ኦነጋዊያንን አሰልጥኗል፤ዐማራውን እንዲጨፈጭፉ መርቷል ድጋፍም ሰጥቷል። በአሁኑ ወቅት ራሱን ለማዳን የሚፍጨረጨረው ትህነግ ዐማራውን ይጨፈጭፋል ብሎ ማለት አይቻልም። ዐማራውንየሚጨፈጭፉት ትህነግ መሰል ኦነጋዊያን ናቸው።

4.የኦሮሚያና የፌደራሉ መንግሥታት በተናጠልም ሆነ በጋራ የዐማራውን ሕዝብ ደህንነት ማስጠበቅ ያልቻሉበት መሰረታዊ ምክንያት አቅም ስለሌላቸው ወይንስ እነሱም የሴራው ተባባሪ በመሆናቸው ነው?

5. የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በአማራው ላይ ተደጋጋሚ ዕልቂት በተከሰተባቸው አካባቢዎች፤ በተለይ በምእራብና ምስራቅ ወለጋ ለምን ጠንካራ የፖሊስና የልዩ ኃይል ስምሪት አላደረገም? አቅም ካነሰውም ለምን የፌደራል መንግስቱን በግልፅ አልጠየቀም?

6. የፌደራል መንግስቱስ የዜጎችን ደህንነት ለመጠበቅ ለምን ስጋት ካለባቸው አካባቢዎች ላይ ሰራዊት መድቦ ህዝቡ እንዳይጨፈጨፍ ተገቢ ጥበቃ አያደርግም?

7. መንግስት ለምንድን ነዉ መታጠቅ የሚችሉ አማሮችን ሁሉ በማስታጠቅ እራሳቸዉንና የአካባቢውን ማህበረሰብ ደህንነት እንዲጠብቁ የማያደርገዉ?

8. መንግሥት ለምንድን ነዉ በአማራው ላይ እየደረሰ ያለውን ግልፅ የሆነ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ በመንግስት ሚዲያ የማያወግዘዉ?

9. ለምንድን ነው መንግስት ጭፍጨፋውን የሚያደርሱትን የተደራጁ አካላት ለህግ የማያቀርበው?

10. በኦሮሚያ ፣መተከል ብሎም በመላው ኢትዮጵያ ንፁሃን አማራወች በራሳቸው አገር በግፍ መጨፍጨፋቸው መቼ ነው የሚቆመው?

11. እንዲሁም ደግሞ ካለፈዉ ሳምንት ጀምሮ ኦነግ ከኦሮሚያ የመንግስት መዋቀር የሚደረግለትን ሁለተናዊ ድጋፍ በመጠቀም በሰሜን ሸዋ፡ በአጣዬ ፣ ማጀቴ ፣ ሸዋ ሮቢትና አካባቢዉን በመዉረር ህፃናትና ሴቶች ሳይቀሩ በአማራዉ ላይ እያደረሰ የሚገኘዉን መጠነ ሰፊ ጭፍጨፋና የሺብር ዘመቻ በፅኑ እናወግዛለን። የፌደራል መንግስት በአስቸኳይ እርምጃ እንዲወስድ እንጠይቃለን። የኢትዮጵያ ህዝብም ይህን የኦነግ የሺብር ዘመቻ አጥብቆ እንዲያወግዘዉ ጥሪ እናቀርባለን።

ለእነዚህ ጥያቄወች አፋጣኝ መልስ በመስጠት መንግስት የወንጀሉ ተባባሪ አለመሆኑን ማሳየት ይጠበቅበታል:: ይህን ካላደረገ ብ/ጀ/ል ከማል ገልቹ በአንድ ወቅት ኤል ቲቭ ለተባቴሌቪዥን ጣቢያ ባደረጉት ቃለ ምልልስ ያሉትን እውነትነ

ቱን ያረጋግጥልናል ማለት ነው። እንዲህ ብለው ነበር :"የአማራን ህዝብ ግድያና ሞት የዐብይ መንግስት ስለሚፈልገዉ እንጂ ማስቆም አቅቶት አይደለም::መንግስት አቅም አለዉ::ህዝብ እየጨፈጨፈ ነዉ የሚባለዉን ሀይል በጉልበት ወይ ም በድርድር ሙሉ ለሙሉ ሊያቆመዉ ይችላል::አዲስ አበባ ላይ የኦነግ አመራር የሚባሉትን ተንከባክቦና አቅፎ በመያዝ እነዚህ መሪዎች የሚያዙት ሰራዊት ሰዉ ይጨፈጭፋል ብሎፕሮፖጋንዳ መስራት ሀላፊነት የጎደለዉ ነገር ነዉ::መሪዎቹተጠያቂ መሆን ሲገባቸዉ መሪዎቹን ተጠያቂ ያላደረገዉ መንግስት በተጨባጭ የህዝቡን ግድያ እራሱ ለፕሮ ፖጋንዳ ስለሚፈልገዉ ነዉ":: ይህን የጄኔራሉን ግልፅ የሆነ ትንተና የሚሺር ስራ ከክልሉ መንግስትም ሆነ ከፌደራል መንግስት በአስቸኳይ እንጠብቃለን::

እኛ በውጭ የምንገኝ የአማራ ነገድ ተወላጆችበኢትዮጵያዊነታችን የማንደራደር በአማራነታችንም እጅግየምንኮራ ስን ሆን በኢትዮጵያ በተለይም በኦሮሚያ ክልል በአማራው ላይ እየተካሄደ ያለውን የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋዝም ብሎ ማ የትና መስማት ከአቅማችን በላይ ሆኖብናል:: ለማጠቃለል ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግስትና ለፌደራል መንግስት አስቸኳይ መፍትሄ የሚሹ የሚከተሉትን ጥያቄወች እናቀርባለን።

1.በክልሉ የሚኖሩ አማሮች በህይወት የመኖር ዋስትና እንዲሰጥ

2. ራሳቸውን ለመጠበቅ የገዙትን የተወረሰባቸው መሳሪያ በአስቸኳይ እንዲመለስላቸው እንዲሁም መታጠቅ ለሚችሉ መንግስት አሰልጥኖ እንዲያስታጥቃቸው

3.የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋውን የሚያቀነባብሩትን የሚመሩትንና የሚፈፅሙትን በአስቸኳይ ለህግ እንዲያቀርብ

4. የተፈናቀሉ አማሮች ወደ መኖሪያ ቀያቸው እንዲመለሱ ለጠፋው ህይወትና ንብረት ከመንግስት ተገቢውን ካሳ እንዲያገኙ

5. ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ልክ አማራ ክልል እንዳደረገው የኦሮሚያ ክልል በክልሉ ለሚኖሩ ለአማሮችም ሆነ ለሌሎችኢትዮጵያውያን ራሳቸውን ለማስተዳደር የሚያስችሉመዋቅሮች እንዲኖራቸው እን ዲያደርግ፣

እኛ እየጠየቅን ያለዉ መንግስት ዋነኛ ተግባሩን እንዲወጣ ነዉ። ይኸዉም የዜጎችን በህይወት የመኖር መብት ማረጋገጥ። ይህንን እዉነታ ዶክተር ወዳጄነህ መሃረነ ባማረ መልኩ እንደዚህ አድርጎ ገልፆታል።

“ልማቱ ይቅርና የሚታረዱ ህጻናትን እና አዛውንቶችን ብቻ ታደጉልን። ሊበቃ ይገባል።Stop the bleeding! Stop the bloodshed!! ይህ መረጃ እንደሚደርሳችሁ አውቃለሁ። የሚፈሰውን ደም ማቆም አለባችሁ። የሚታረዱትን ሰዎች ደ ም ማቆም ካልቻላችሁ አበባብትነሰንሱ ፣ ሽቶ ብታርከፈክፉ ጉዳያችን አይደለም።አይቻልም ልትሉ ትችላላችሁ። ሙስጠፌ ችሏል። በጣም ያስፈራየነበረንን ዘመን አሳልፎናል። እናንተም ሌላውን ነገር ተውት ካስፈለገ። ልማቱም እድገቱም ይቅር። የሚታረዱትን አሮጊቶች አድኑ!! የሚታረዱ ህጻናትን አድኑ። This is your primary responsibility! በጣም ደከመን ሰለቸን። ጨለማ ቀን፣ሳምንት ፣ወር ይሰለቻል። የወረዳ አስተዳዳሪዎች ቆማችሁ ገጀራ የምታቀብሉ እግዚአብሄር ይፈርድባችኃል፣ የትም አታመልጡ፣ከሰው ብታመልጡም ስለዚህ ይብቃን። ካስፈለገ ሌላውን ስራችሁን ተውትና አሮጊትእና ህጻናት የሚያርዱትን ሰዎች ያዙ።”

ይህ ሳይሆን ቀርቶ ይህ የለየለት በአማሮች ላይ በማንነት ያነጣጠረ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ(genocide) ከቀጠለ አጥብቀን የምናወግዘውና የምንታገለው ጉዳይ ሲሆን ይህ ከመጠን ያለፈ የዘር ዕልቂት በአስቸኳይ ለማስቆም የዓለም አቀፍ ጠበቆች ቀጥረን የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች ላ ይ ክስ ለመመሥረት እንገደዳለን::ይህ ከመሆኑ በፊት ግን ከክልሉና ከፌደራሉ መንግስትአስቸኳይ ተገቢ ምላሽ እንጠ ብቃለን::

ግልባጭ

ለኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት፣ ወ/ሮ
ሣህለወርቅ ዘውዴ
ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ
ለኢፌዴሪ ም/ጠቅላይ ሚ/ርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አቶ ደመቀ መኮንን
ለአቶ ገዱ አንዳርጋቸው፤ የጠ/ሚ/ር የደህንነት አማካሪ

ለኢፌዴሪ ሰብአዊ ኮሚሽን ኮሚሺነር ዶ/ር ዳንኤል በቀለ
ለኢፌዴሪ የፌዴሬሺን ምክር ቤት ሰብሳቢ አቶ አደን ፋራህ
ለኢፌዴሪ የተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ
ለኦሮሚያ ክልል ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ
ለአማራ ክልል ተወካዮች ምክር ቤት፣ አፈ ጉባኤ፣
ለአቶ አገኘሁ ተሻገር፣ የአማራ ክልላዊ
መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር
ለክቡር አምባሳደር ፍጹም አረጋ፤ የኢትዮጵያ አምባሳደር፤ ዋሺንግተን ዲሲ፤
ለዶር ገበያው ጥሩነህ የአማራ ምሁራን መማክርት ጉባኤ
ሊቀ መንበር፤ ባህር ዳር፤ ኢትዮጵያ

ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ከተደቀነባት የህልዉና አደጋ ቸሩ እግዚሀቤር ይጠብቃት።
ኢትዮጵያ በሕዝቧ አንድነትና ወንድማማችነት ታፍራና ተከብራ ለዛላለም ትኑር።

ዶ/ር አምባቸዉ ወረታዉ
ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት ሊቀመንበር